በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

የመካነ ቅዱሳን አ.ያቄም ወሀና ቤተ ክርስቲያን

የወልድ ዋሕድ ሰ/ት/ቤት

ትምህርተ ሰዋስው ዘልሳነ ግእዝ ማስተማሪያ

የትምህርት መግለጫ/course syllabus)

ሠሌዳ ዘጊዜ /Schedule/	**መንፈቅ ፩** /Semistor one/	**ዓመት ፳፻፲፮** Year 2023	**ክፍለ ትምህርት** **ለ……ክፍል…….** For…….Section…….
የትምህርት ርእስ /Cource title/	**ትምህርተ ሰዋስው ዘልሳነ ግእዝ ፩** /Geez I/		**ዐበይ ሰዓት ፫** /3 credited hours/
የመምህሩ መግለጫ /Descriptions/	**ጳውሎስ ብርሃኔ ዘሪሁን**/Pawlos Birhanie Zerihun/ **የቅኔና የግእዝ ቋንቋ መምህር(ከሊቀ ሊቃውንት ያሬድ ሽፈራው ፣ ጨጎዴ ሀና)** BA Degree in Geez Language and Literature From Holy Trinity University BA Degree in Development Studie From Haramaya University MA Degree in Bussines Administration From Yardistck International College MA Candidate in Geez Language and Literature From Holy Trinity University		
የመምህሩ አድራሻ/Adress	**አዲስ አበባ** /Addis Ababa/ **ስልክ ቁጥር**/Phone/ 09-15-64-25-85 Email: pawlosbirhanie@gmail.com Telegram: https://t.me/+fKrXjO6FiPM1Mjg0 (Geez Language Education)		
የሚሰጠው ትምህርት መግለጫ	➢ **ስለ አርእስተ ግስ ፣ አዕማደ ግስና አሥራው ግስ** ➢ **ስለ መራሕያን ፣ አመልካች ቅጽሎች ፣ የወገን ቅጽል** ➢ **ስለ ዘርፍ ፣ ዘርፍ አየያዥ ፣ዘርፍ ደፊ ፣ ዘርፍ ጠምዛዥ** ➢ **ስለ ዝርዝር ፣ ገቢር ና ተገብሮ** ➢ **ስለ አካል ክፍሎች** ➢ **ስለ የዋህና መሠርይ ግስ ርባታ**		

Geez Language

	ከላይ የተዘረዘሩትን አርእስቶች በምሳሌ አስደግፈን እንማማራለን ።
የትምህርቱ መሰረታዊ ዐላማ /General Objective/	የዚህ ትምህርተ ሰዋስው ዘልሳነ ግእዝ ትምህርት መሰረታዊ ዓላማ ተማሪዎች በግእዝ ቋንቋ ዐረፍተ ነገር መስራት እንዲችሉ ፣ መተርጎም እንዲችሉ እና ማሰሪያ አንቀጹን እስከ ባለቤቱ ፣ እስከ ተሳቢው ለይተው እንዲየውቁ ማስቻል ነው ።
የትምህርቱ ዝርዝር ዐላማወች /Specific Objectives/	ተማሪዎች ይህንን የትምህርት ዝግጅት ሲያጠናቅቁ ➢ ግስም ሆነ ዝርዝር ስም ባለቤቱን ለይተው ያውቃሉ ። ➢ ቅጽልን ፣ ዘርፍን ፣ ዝርዝርን ተጠቅመው ዓረፍተ ነግር ይሰራሉ ። ➢ የዋህና መሠርይ ግስ ከቀዳማይ እስከ ትእዛዝ ርባታዉን ውቃሉ ።
የመገምገሚያ ስልቶች /Evaluation Methods/	የትምህርቱ መመዘኛዎች <u>በፐርሰንት</u> ➢ ፲፭ (15%) የክፍል ክትትል(for class attendance) ➢ ፲፭ (15%)አጋማሽ (mid)ፈተና ➢ ፳ (20) ግብረ ቤት (assignment) ➢ ፶(50%)የማጠቃለያ (final) ፈተና ፤ አጠቃላይ/Total/ 100%
ማጣቀሻ መጻሕፍቶች /References/	• ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ፣መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበቃላት • ሀብተ ማርያም ወርቅነህ (ሊ/ሥ)(1963)ጥንታዊ የኢትዮጵያትምህርት ፤ ብርሃንና ስላም ማተሚያቤት አዲስ አበባ • ያሬድ ሽፈራው ሰዋስው ወግስ (2005) ባሕርዳር ጊዮርጊስ ማተሚያ ቤት • ዘርዐ ዳዊት አድሐኖመርኖ ሰዋስው ዘልሳነ ግእዝ(2008) • ዶ/ር አዲስ ተኩነህ(2006) መሠረተ ግእዝ ፣ • ደሴ ቀለብ(ትንሣኤ ግእዝ) ፣አዲስ አበባ(2007) • መ/ር ዐቢይ ቤዛ(2010) ፣ ዐምደ ግእዝ • ሊቀ ጎሩን በላይ መኮንን(2002) ፣ሕያው ልሳን

GeezLanguage

መክሥተ አርእስት

መክሥተ አርእስት iii

መግቢያ 1

ክፍል አንድ 4

፩.፩. የግስ አርእስትና አሥራወ ቀለማት 4

፩.፪. የግስ አርእስት 4

፩.፫. አዕማደ አርእስት 6

፩.፬. ዐመላተ አሥራወ ቀለማት 6

ክፍል ኹለት 9

፪.፩.መራሕያን /አጻፋዎች/ተውላጠ ስሞች/ 9

፪.፪. አመላካች ቅጽሎች 9

፪.፪.፩. የመራሕያን እና አመላካች ቅጽሎች አገልግሎት 10

፪.፪.፪. የአመላች ቅጽሎችና የመራሕያን ልዩነት 11

፪.፫. ወገናዊ ቅጽሎች 11

ክፍል ሦስት 12

፫.፩. ዘርፍ አየያኾና ዘርፍ ደፊ 12

፫.፪. ዘርፍ ጠማዛኾ 13

ክፍል አራት 14

፬.፩. ዝርዝር ፣ገቢርና ተገብሮ 14

፬.፪. የአካል ክፍሎች 16

፬.፫. ርብሐ የዋህ ወመሠርይ ግስ 17

Geez Language

መግቢያ

ቋንቋ ማለት ለሰማዕያን በጽሑፍም ኾነ በቃል መግባቢያ ፣ መነጋገሪያ ፣ ሐሳብ መለዋወጫ ወዘተ …… ማለት ነው ። ሕዝብና ቋንቋ የአንድ ሳንቲም ኹለት ገጽታዎች ናቸው ። አይነጣጠሉም ማለትም ያለ ሕዝብ ቋንቋ የለም ። ያለ ቋንቋ ደግሞ ሕዝብ ሊኖር አይችልም ። ከብዙ ቋንቋዎች ውስጥ የግእዝ ቋንቋ አንዱና ዋነኛው ነው ።

ግዕዝ ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን መቀራረብ /ዝምድና/ ስናይ ነገደ ዮቅጣን /ዘፍ ፲ ÷ ፳፭-፴፪/ በሦስት ሺህ አምስት መቶ አሥር ዓ.ዓ በኢትዮጵያ ሰፍረው ነገደ ዮቅጣን አግዓዝያን ተብለው አገራቱም ብሔረ አግዓዚ ተብላ እንደተጠራች ታሪክ ያሰረዳል ።

በኢትዮጵያ በግእዝ ቋንቋ የተጻፉ በርካታ የኢትዮጵያ ሕዝብ እውነተኛ ታሪክን ፣ ባህልን ፣ ማንነትን የሚገልጹ መጻሕፍት አሉ ። መጻሕፍቱን ለመማርም ኾነ ለማስተማር እና በውስጣቸው ያለውን ምሥጢር ለማወቅ የግእዝ ቋንቋ ማጥናት ተገቢ ነው ። ቋንቋውን ለማጥናትና ለማወቅ ደግሞ የቋንቋው የጀርባ አጥንት የኾኑትን አገባቦች ፣ ቋንቋው የተመሠረተበትን ግሶችና ርባ ቅምሮች ፣ ቋንቋውን ከሌሎች ቋንቋዎች ለየት የሚያደርጉትን ባሕርያት…ማጥናት ለኹሉም አስፈላጊ ነው ።

- **የቋንቋ ዓላማ**

አጠቃላይ የቋንቋ ዓላማዎች ስድስት ሲሆኑ ከዚህ በታች እንደሚከተለው በአጭሩ ይቀርባሉ ።

- የማድመጥ ችሎታን ማሳደግ
- የመናገር ችሎታን ማሳደግ
- የማንበብ ችሎታን ማሳደግ
- የመጻሐፍ ችሎታን ማሳደግ
- የስነ ጽሑፍ እውቀትን ማዳበር
- የስነ ልሳን እውቀትን ማዳበር … ናቸው ።

ከአራቱ የቋንቋ ክህሎት ሁለቱ ማለትም

- ✓ የማድመጥና የማንበብ ክህሎት መረጃ ለመሰብሰብ ይጠቅማሉ
- ✓ የመናገር እና የመጻሐፍ ክህሎት ደግሞ ለሌላው መረጃ ለመስጠት የሚጠቅሙ ናቸው ።

❖ **የቋንቋ ባህሪያት ፡-**

የቋንቋ ባህሪያት በርካታ ቢሆኑም ለማሳያ ያህል ከዚህ በታች የቀረቡትን በአጭሩ እንመልከት

ሀ/ ቋንቋ ዘፈቀዳዊ ነው ፡ ቋንቋ ዘፈቀዳዊ ነው ስንል አንድ ቋንቋ የሚጠቀምባቸውን ድምጾች ፣ ለነገሮች የተሰቱትን ስያሜዎች እዲሁም ቋንቋ ያሉትን የሰዋስው ሕጎች ሰዎች ሆን ብለው አስበው የፈጠሯቸው አለመሆናቸውን መግለጽ ነው ፡፡ በቋንቋ አገልግሎት ላይ በዘፈቀደ የዋሉት ድምፆች ፤ ለነገሮች የተሰጡት ስያሜዎች እና የተፈጠሩት መዋቅሮች አንዴ ሥርዓት ከተበጀላቸው በኃላ ያንኑ ሥርዓት ይከተላሉ እንጂ ተፋልሶ አይታይባቸውም ።

ለ/ ቋንቋ ሥርዓታዊ ነው ፡ የቋንቋው ተናጋሪ ሕብረተሰብ የተቀበለው ወይም የሚሰማማበትን የቋንቋውን ድምጾች በመጠቀም ፤ ድምጾች በሆኔያት ተወክለው ቃላትን ፤ ቃላት ተቀናጅተው ሐረጋትን ፤ ሐረጋትን ተቀናጅተው ዐረፍተ ነገሮችን ፤ ዐረፍተ ነገሮች ተቀናጅተው አንቀጽን ፤ አናቅጽ ተቀናጅተው ድርሰትን እንዴት እንሚመሰርቱ የአወቃቀር ህግ እንዳለው መግለጽ ነው ።

ሐ/ ቋንቋ ሰዋዊ ነው ፡ እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ከ22ቱ ሥነ ፍጥራታት መካከል የራሱ የሆነ ቋንቋ ያለው በቋንቋ የሚግባባ የሰው ልጅ ስለሆነ ቋንቋ በባህሪው ሰዋዊ ነው ።

መ/ ቋንቋ የሚወለድ ፤ የሚያድግ ደግሞም የሚሞት ነው ፡ የሰው ልጅ የቋንቋ ባለቤት ሆኖ በመጣበት ሐብቱ/ጸጋው ይለምደዋል ፤ በንግግር ፤ በጽሑፍ ኮትኩቶ ያሳድገዋል ፤ አይጠቅመኝም ፤አይረባኝም ሲል ደግሞ ይተወዋል ቋንቋውም በዚህ ጊዜ ይሞታል ፡፡

ሠ/ ቋንቋ ይለመዳል- ቋንቋ ባደገ እንጂ በተወለደ አይደለም ፡፡ ማንኛውም ሰው ማንኛውንም ቋንቋ መልመድ ፤ መናገር ስለሚችል ቋንቋ በባህሪው ይለመዳል ፡፡

❖ **የቋንቋ ጥናት ጠቀሜታ**

ሀ/ ቋንቋ መረጃ ሰጪ ነው ፡ ቋንቋ መረጃ ሰጪ ነው ስንል ቋንቋ መረጃ ለመስጠት ፤ ለመቀበልን የሚጠቅም መሳሪያ መሆኑን ያሳያል ። ለምሳሌ ቋንቋን አስተያየት ፤ምክር ለመስጠት ፣ንግግር ለማድረግ ስንጠቀምበት መረጃ እየሰጠን ሲሆን በሌላ መልኩ ቋንቋን ጥያቄ ለመጠየቅና ለመረዳት ስንጠቀምበት መረጃ ለመቀበል መጠቀማችንን ያሳያል ።

Geez Language

ለ/ ቋንቋ ገላጭ ነው ፡ ቋንቋ ሐሳቦችን እና ስሜቶችን ይገልፃል ። የቋንቋ ገላጭነት ማንኛውንም መረጃ ሊያካትት ይችላል ፡ ፡ ምክንያቱም የቋንቋ ገላጭነት ዓላማው ስሜትን ሀሳብን ማስተላለፍ ነው ። የቋንቋ ገላጭነት በሥነ ጽሑፍ ፣ በሙዚቃ እና በትወና ጥበብ ማሳየት ይቻላል ።

ሐ/ ቋንቋ መመሪያ ሰጪ ነው ፡ ቋንቋ ማህበራዊ ሥርዓትን ለማስፈን ፤ በሥርዓቱም ለመጠበቅ ይጠቅማል ። ቋንቋ በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ የሚጠበቁ መመሪያዎችን ፤ ደንቦችን ያወጣል ። መመሪያን የጠበቀ ምን እንደሚያገኝ ከመመሪያ ውጭ የሆነ ምን እንደሚገጥመው ይወስናል ።

- **ቋንቋዎች የመለያየት ምክንያት**

በዓለም በአንድ ወቅት (ዘመን) ወይም ከዛሬ 7000 ሺህ ዓመት አስቀድሞ በዓለም የሰው ልጅ የሚጠቀምበት አንድ ቋንቋ ነበር ። በጊዜ ብዛት ቋንቋ ከአንድ ወደ 7000 ቋንቋዎች ሊከፋፈሉ ችለዋል ። ለቋንቋዎች መለያየት/መከፋፈል ምክንያቶቹ ብዙ ናቸው ።

- ✓ በሰው ልጅ አለመታዘዝ ምክንያት/በተአምራት
- ✓ በቋንቋዎች ላይ በሚደረግ የመዋቅር ፤ የይዘት የማሻሻያ ስራ
- ✓ ቋንቋዎች ከተግባቦት ቋንቋነት ወጥተው ወደ ጽሑፋዊነት ቋንቋ ብቻ እንዲመጡ በሚደረገው ሽፍጥ...ወዘተ በዋናነት ይጠቀሳሉ ።

እንዲህ ያለውን ቀደምት የቋንቋ አከፋፈል ታሪክን የሚያጠና ሳይንስ በስነ ልሳን ተመራማሪ ሊቃውንት ዘንድ **የፕሮቶ ላጉች** (Proto Language) ፍለጋ ጥናት ይሉታል ።

- **የትምህርቱ ጠቀሜታ**
  - በግእዝ ቋንቋ የተጻፉትን መጻሕፍት አንብቦ ምሥጢራቸውን ለመረዳት
  - የግእዝ የቃልና የሰዋስው አወቃቀር ባሕርያት ለመገንዘብ ይረዳል
  - ግእዝ በኢትዮጵያ ለሚገኙ ሴማዊ ቋንቋዎች አባት መሆኑን ያስረዳል
  - በግእዝ ቋንቋ ውይይት ፣ ንግግርና በአጠቃለይ ተግባቦት ለማድረግ
  - በግእዝ ቋንቋ ዙሪያ ጥናት ለሚያካሂድ ተመራማሪ ለምርምር ተግባሩ ግባት በመሆን ይጠቅማል

Geez Language

ክፍል አንድ

አርእስተ ግስ ፣ አዕማደ ግስና አሥራው ግስ

፩.፩. የግስ አርእስትና አሥራው ቀለማት

፩.፪. የግስ አርእስት

የግእዝ ቋንቋ በዋናነት መሠረቱ ግስ ወይም አንቀጽ ነው ። ግስ በሚረባበት ወይም በሚገሰስበት ጊዜ ገቢር ወይም ሳቢ የኾነ ግስ ኹሉ አምስት አዕማድ አሉት ። እነሱም አድራጊ ፣ አሰደራጊ ፣ አዳራጊ ፣ ተደራጊና ተዳራጊ ናቸው ። በተመሳሳይ ግስ በሚገሰስበት ጊዜ የኀላፊ ጊዜ ግስ ፣ የትንቢት ጊዜ ግስ ፣ የዘንድ ጊዜና የትእዛዝ ጊዜ ግስ ኹኖ ይገሰሳል ።

የግስ አርእስት ቀለማት

‹‹**አርእስት**››ማለት ርእሰ አለቃ ኾነ ከሚለው የግእዝ ቃል የተወሰደ ሲሆን **ርእስ** ማለት አለቃ ፣ መሪ ፣ አዛዥ ማለት ነው ። **አርእስት** ብዛት ነው ። ትርጓሜውም አለቆች ፣ መሪዎች ፣ አዘዦች ማለት ነው ። አጠቃላይ ከ"ሀ"እስከ "ፐ"ድረስ የሚገኙ አንቀጾች(ግሦች) የሚገሠሡት ወይም የሚነገሩት በእነርሱ ሥር ስለሆነ ‹‹**የግስ አርእስት**››የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል ። **የግስ አርእስት ቀለማት ስምንት ናቸው ፤ ፤እነሱም ፡-**

ተ.ቁ	አንቀጽ	ትርጓሜ	ምኅፃረ- ቃል
1	ቀተለ	ገደለ	ቀተ
2	ቀደሰ ("ደ"ይጠብቃል)	አመሰገነ	ቀደ
3	ተንበለ	ለመነ	ተን
4	ባረከ	ባረከ	.ባረ
5	ማሕረከ	ማረከ	ማሕ
6	ሴሰየ	መገበ	ሴሰ
7	ክህለ	ቻለ	ክህ
8	ጠመረ	ጻፈ	ጠመ

ከላይ ለተዘረዘሩት የግስ አርእስቶች ለእያንዳንዳቸው ሠራዊቶች አሏቸው ። ከዚህ ቀጥለን አርእስቶችን ከሠራዊቶቻቸው እናሳያለን ።

የቀተለ ሠራዊቶች	**የሴሰየ ሠራዊቶች**
አንቀጽ ትርጓሜ	**አንቀጽ ትርጓሜ**
ሀ. ጎቤተ.....አገለገለ	ሀ. አሌለየ.....ማለደ
ለ. ተኬሰ.....መታ	ለ. አንጌገየ.....ተቅበዘበዘ
ሐ. ሰኮተ.....ወለወለ	ሐ. አቅዜዘየ.....ቅዝዝ ቅዝዝ አለ
የቀደሰ ሠርዌ አንድ ብቻ ነው	**የጠመረ ሠራዊቶች**
አንቀጽ ትርጓሜ	**አንቀጽ ትርጓሜ**
ሀ. አንገለገ.....አከማቸ	ሀ. አልሖሰሰ.....ሾክ ሾክ አለ
የተንበለ ሠራዊቶች	ለ. አክሞሰሰ.....ፍግግ ፍግግ አለ
አንቀጽ ትርጓሜ	ሐ. ሶርየመ.....አገመ
ሀ. ቀበያውበጠ.....ቀላወጠ	መ. ጎርዔመ.....ጉርድ አወጣ
ለ. ቀንጦሰጠ.....ተሰለፈ/አሰለፈ	**የባረከ እና የከሀለ**
ሐ. ዘርዜቀ.....ነፋ	ራስ ራሳቸውን ከመሳሰለ በስተቀር ሌላ ዐመል ያለው ግሥ አይገኝላቸውም ወይም የላቸውም ።
የማሕረከ ሠራዊቶች	
አንቀጽ ትርጓሜ	
ሀ. አንቃዕደወ.....አንጋጠጠ	
ለ. ሰካዕለወ.....ቆጠቆጠ	
ሐ. አናሕሰየ.....አቃለለ	

Geez Language

፩.፫. አዕማደ አርእስት

1. ቀተለ……ገደለ……አድራጊ
2. ተቀትለ……ተገደለ……ተደራጊ
3. አቅተለ……አስገደለ……አስደራጊ
4. ተቃተለ……ተገዳደለ……ተዳራጊ
5. አስተቃተለ……አገዳደለ……አዳራጊ

፩.፬. ዐመላተ አሥራው ቀለማት

(ሀ) በቀደሰ ቤት በ‹‹ሀ››ወይም በ‹‹አ›› የተነሣ ግስ አሥራው ፊደሉ ግእዝ ይኾናሉ ።

ቀዳማይ	ፍቺ	ካልኣይ	ፍቺ	ዘንድ	ፍቺ	ትእዛዝ	ፍቺ
ገየለ	በረታ	ይጌይል	ይበረታል	የገይል	ይበረታ ዘንድ	የገይል	ይበርታ
ሐወጸ	ጎበኘ	ይሔውጽ	ይጎበኛል	የሐውጽ	ይጎበኝ ዘንድ	የሐውጽ	ይጎብኝ
ሐገገ	ሕግ ሠራ	ይሔግግ	ሕግ ይሠራል	የሐግግ	ሕግ ይሠራ ዘንድ	የሐግግ	ሕግ ይሥራ
አዘለ	በረታ	ይኤዝል	ይበረታል	የአዝል	ይበረታ ዘንድ	የአዝል	ይበርታ
ዐለገ	ሰለበ	ይዔልግ	ይሰልባል	የዐልግ	ይሰልብ ዘንድ	የዐልግ	ይስለብ
አመጸ	በደለ	ይኤምጽ	ይበድላል	የአምጽ	ይበድል ዘንድ	የአምጽ	ይበድል
አመረ	አመላከተ	ይኤምር	ያመላክታል	የአምር	ያመላክት ዘንድ	የአምር	ያመላክት

(ለ) በቀተለ ቤት ፪ ወይም ፫ ፊደል ኹኖ በ‹‹ሀ››ወይም በ‹‹አ››የተነሣ ግስ አሥራው ፊደሉ በትንቢት ግእዝ ፣በዘንድና በትእዛዝ ሳድስ ነው

ቀዳማይ	ፍቺ	ካልኣይ	ፍቺ	ዘንድ	ፍቺ	ትእዛዝ	ፍቺ
ሐዘነ	አዘነ	የሐዝን	ያዝናል	ይሕዝን	ያዝን ዘንድ	ይሕዝን	ይዘን
ሀመለ	ለቀመ	የሀምል	ይለቅማል	ይህምል	ይለቅም ዘንድ	ይህምል	ይልቀም
ሀሠለ	ለበበ	የሀሥል	ይለባል	ይህሥል	ይለብ ዘንድ	ይህሥል	ይልበብ
ሀነቀ	አነቀ	የሀንቅ	ያንቃል	ይህንቅ	ያንቅ ዘንድ	ይህንቅ	ይነቅ
ያደ	ዞረ	የዐውድ	ይዞራል	ይዐድ	ይዞር ዘንድ	ይዐድ	ይዙር
አየየ	ዞረ	የአይይ	ይዞራል	ይእይይ	ይዞር ዘንድ	ይእይይ	ይዙር
አምነ	አመነ	የአምን	ያምናል	ይእምን	ያምን ዘንድ	ይእምን	ይመን

Geez Language

(ሐ) በቀተለ ቤት በ‹‹ወ››ወይም በ‹‹ው›› የተነሣ ግስና በመካከሉ ‹‹ሀ››ወይም ‹‹አ›› ያሉበት ግስ ሲረባ አሥራው ፊደሉ በዘንድናበትእዛዝ ግእዝ ይኾናል ።

ቀዳማይ	ፍቺ	ካልኣይ	ፍቺ	ዘንድ	ፍቺ	ትእዛዝ	ፍቺ
ወሐየ	ጎበኘ	ይዋሒ	ይጎበኛል	የሐይ	ይጎበኝ ዘንድ	የሐይ	ይጎብኝ
ወሀበ	ሰጠ	ይሁብ	ይሰጣል	የሀብ	ይሰጥ ዘንድ	የሀብ	ይስጥ
ውሕደ	ጎደለ	ይውሕድ	ይጎላል	የሐድ	ይጎድል ዘንድ	የሐድ	ይጉደል
ውሕጠ	ዋጠ	ይውሕጥ	ይውጣል	የሐጥ	ይውጥ ዘንድ	የሐጥ	ይዋጥ
ውዕለ	ዋለ	ይውዕል	ይውላል	የዐል	ይውል ዘንድ	የዐል	ይዋል
ወሐከ	አነሣሣ	ይውሕክ	ያነሣሣል	የሐክ	ያነሣሣ ዘንድ	የሐክ	ያነሣሣ
ውእየ	ተቃጠለ	ይውኢ	ይቃጠላል	የአይ	ይቃጠል ዘንድ	የአይ	ይቃጠል

(መ) በተንበለ ቤት በ‹‹ሀ››ወይም በ‹‹አ›› የተነሣ ግስ ሲረባ አሥራው ፊደሉ በትንቢት ፣በዘንድና በትእዛዝ ግእዝ ይኾናል ።

ቀዳማይ	ፍቺ	ካልኣይ	ፍቺ	ዘንድ	ፍቺ	ትእዛዝ	ፍቺ
ሐንከሰ	አነከሰ	የሐነክስ	ያነክሳል	የሐንክስ	ያነክስ ዘንድ	የሐንክስ	ያንክስ
ጎርበደ	ተስበደበደ	የጎረብድ	ይስበደበዳል	የጎርብድ	ይስበደበድ ዘንድ	የጎርብድ	ይስበድበድ
ሐይመነ	አሳመነ	የሐየምን	ያሳምናል	የሐይምን	ያሳምን ዘንድ	የሐይምን	ያሳምን
ሐውከከ	አጎደለ	የሐወክክ	ያጎድላል	የሐውክክ	ያጎድል ዘንድ	የሐውክክ	ያጉድል
አንበዘ	ልብ አሳጣ	የአነብዝ	ልብ ያሳጣል	የአንብዝ	ልብ ያሳጣ ዘንድ	የአንብዝ	ልብ ያሳጣ
አንዘረ	መታ	የአነዝር	ይመታል	የአንዝር	ይመታ ዘንድ	የአንዝር	ይምታ
አንብዐ	አለቀሰ	የአነብዕ	ያለቅሳል	የአንብዕ	ያለቅስ ዘንድ	የአንብዕ	ያልቅስ

(ሠ) በ‹‹አድራጊ››ወይም በ‹‹አስደራጊ›› የተነሣ ግስ አስራው ፊደሉ ራብዕ ይኾናል ።

ቀዳማይ	ፍቺ	ካልኣይ	ፍቺ	ዘንድ	ፍቺ	ትእዛዝ	ፍቺ
አፍቀረ	ወደደ	ያፈቅር	ይወዳል	ያፍቅር	ይወድ ዘንድ	ያፍቅር	የውደድ
አግመረ	ቻለ	ያገምር	ይችላል	ያግምር	ይችል ዘንድ	ያግምር	ይቻል
አሥመረ	አገለገለ	ያሠምር	ያገለግላል	ያሥምር	ያገለግል ዘንድ	ያሥምር	ያገልግል
አመሠጠረ	አራቀቀ	ያመሠጥር	ያራቅቃል	ያመሥጥር	ያራቅቅ ዘንድ	ያመሥጥር	ያራቅ
አንበበ	አነበበ	ያነብብ	ያነባል	ያንብብ	ያነብ ዘንድ	ያንብብ	ያንብ
አርመመ	ዝም አለ	ያረምም	ዝም ይላል	ያርምም	ዝም ይል ዘንድ	ያርምም	ዝም ይበል
አስሐወ	አወለቀ	ያስሐ	ያወልቃል	ያስሐ	ያወልቅ ዘንድ	ያስሐ	ያውልቅ

(ረ) በ‹‹ተደራጊ››ወይም በ‹‹ተደራራጊ››ግስ ሲረባ አስራው ፊደሉ ሳድስ ይኾናል ።

ቀዳማይ	ፍቺ	ካልኣይ	ፍቺ	ዘንድ	ፍቺ	ትእዛዝ	ፍቺ
ተዋነየ	ተጫወተ	ይትዋነይ	ይጫወታል	ይትዋነይ	ይጫወት ዘንድ	ይትዋነይ	ይጫወት
ተደረ	ተመገበ	ይደሮር	ይመገባል	ይደረር	ይመገብ ዘንድ	ይደረር	ይመገብ
ተጋወረ	ተጎራበተ	ይትጋወር	ይጎራበታል	ይትጋወር	ይጎራበት ዘንድ	ይትጋወር	ይጎራበት
ተፍዕመ	ጎረሰ	ይትፍዐም	ይጎርሳል	ይትፍዐም	ይጎርስ ዘንድ	ይትፍዐም	ይጉረስ
ተጋደለ	ተጋደለ	ይታጋደል	ይጋደላል	ይትጋደል	ይጋደል ዘንድ	ይትጋደል	ይጋደል
ተጸምደ	አገለገለ	ይጸመድ	ያገለግላል	ይጸመድ	ያገለግል ዘንድ	ይጸመድ	ያገልግል
ተጻረረ	ተጣላ	ይጸረር	ይጣላል	ይጻረር	ይጣላ ዘንድ	የጻረር	ይጣላ

(ሰ) በአሉታ ጊዜ ‹‹አ››ን መነሻ ሲያደርግ (በአድራጊና በአስደራጊ)አስራው ፊደሉ ከቀዳማይ እስከ ትእዛዝ ‹‹ያ›› ይኾናል ።

ቀዳማይ	ፍቺ	ካልኣይ	ፍቺ	ዘንድ	ፍቺ	ትእዛዝ	ፍቺ
ኢያፍቀረ	አልወደደም	ኢያፈቅር	አይወድም	ኢያፍቅር	አይወድ ዘንድ	ኢያፍቅር	አይውደድ
ኢያቅተለ	አላስገደለም	ኢያቀትል	አያስገድልም	ኢያቅትል	አያስገድል ዘንድ	ኢያቅትል	አያስገድል
ኢያግመረ	አልቻለም	ኢያገምር	አይችልም	ኢያግምር	አይችል ዘንድ	ኢያግምር	አይቻል
ኢያንበረ	አላስቀመጠም	ኢያነብር	አያስቀምጥም	ኢያንብር	አያስቀምጥ ዘንድ	ኢያንብር	አያስቀምጥ
ኢያርመመ	ዝም አላለም	ኢያረምም	ዝም አይልም	ኢያርምም	ዝም አይል ዘንድ	ኢያርምም	ዝም አይበል
ኢያውሥአ	አልመለሰም	ኢያወሥእ	አይመልስም	ኢያውሥእ	አይመልስ ዘንድ	ኢያውሥእ	አይመልስ
ኢያክበረ	አላከበረም	ኢያከብር	አያከብርም	ኢያክብር	አያከብር ዘንድ	ኢያክብር	አያክብር

Geez Language

ክፍል ኹለት

ስመራሕያን ፣ አመልካች ቅጽሎች ፣ የወገን ቅጽል

፪.፩.መራሕያን /አጻፋዎች/ተውላጠ ስሞች/

ውእቱ---እርሱ

አንተ----አንተ

ውእቶሙ--እነርሱ (የሩቅ ወንዶች)

አንትሙ---እናንተ (የቅርብ ወንዶች)

ይእቲ----እርሷ

አንቲ----አንቺ

ውእቶን--እነርሱ (የሩቅ ሴቶች)

አንትን--እናንተ (የቅርብ ሴቶች)

አነ----እኔ (ለአንድ ሴት ወይም ለአንድ ወንድ)

ንሕነ----እኛ (ለብዙ ወንዶችና ሴቶች)

፪.፪. አመላካች ቅጽሎች

ዝ ፣ ዝንቱ-----ይኽ (የቅርብ ወንድ ቅጽል)

ዝኩ ፣ ዝስኩ ፣ ዝክቱ---ያ (የሩቅ ወንድ ቅጽል)

ውእቶሙ ፣ እሙንቱ---እነዚያ (ሩቅ ወንዶች ቅጽል)

እሉ ፣ እሎንቱ---እሊኽ (የቅርብ ወንዶች ቅጽል)

ዛ ፣ ዛቲ---- ይኽቺ (የቅርብ ሴት ቅጽል)

እንትኩ ፣ እንታክቲ---ያች (የሩቅ ሴት ቅጽል)

ውእቶን ፣ እማንቱ--እነዚያ (የሩቅ ሴቶች ቅጽል

እላ ፣ እላንቱ---እሊኽ (የቅርብ ሴቶች ቅጽል)

Geez Language

፪.፪.፩. የመራሕያን እና አመላካች ቅጽሎች አገልግሎት

- **ለባለቤት ቅጽል በመሆን**

ውእቱ ሚካኤል ሊቀ መላእክት--የመካእክት አለቃ እሱ ሚካኤል ነው ።

አንተ አምላክነ አድኅነነ--አንተ አምላካችን አድነን ።

ውእቶሙ እደው ኀያላን--እነርሱ ወንዶች ኃይለኞች ናቸው ።

አንትሙ ጴጥሮስ ወታዴዎስ ሰበክሙ ወንጌለ-እናንተ ጴጥሮስና ታዴዎስ ወንጌልን አስተማራችሁ

ይእቲ ብእሲት ትቀድህ ማየ--እርሷ ሴትዮ ውሃ ትቀዳለች ።

አንቲ ወለት ሠነየ ብኪ--አንቺ ልጂ አማረብሽ ።

ውእቶን መምህራት መሀራ አርድእተ--እነርሱ መምህሮች ተማሪዎችን አስተማሩ ።

አንትን አዋልድ እቀባ ድንግልናክን--እናንተ ቆነጃጂት ድንግልናችሁን ጠብቁ ።

አነ ብእሲት አእመርኩ ፈትለ--እኔ ሴትዮ ፈትልን አወቅኹ ።

አነ መርድእ አእመርኩ ምስጢረ--እኔ ተማሪ ምስጢርን አወቅኹ ።

ንሕነ እደው/አንስት/ ኢንፈርህ ምንተኒ--እኛ ወንዶች/ሴቶች/ምንም አንፈራም ።

- **ባለቤት በመኾን**

ውእቱ አድኅነነ-- እርሱ አዳነን

አንተ እቀበነ--አንተ ጠብቀን

ውእቶሙ ነበሩ--እነርሱ ተቀመጡ(ወንዶች)

አንትሙ አርምሙ--እናንተ ዝም በሉ(ወንዶች)

ይእቲ ትመጽእ--እርሷ ትመጣለች

አንቲ ንዒ--አንቺ ነይ

አነ ኢየአምር ሐሜተ--እኔ አሜት አላውቅም

ንሕነ ኢንጼአቅ--እኛ አንጨነቅም

ማስታወሻ ፡- አመላካች ቅጽሎችም ልክ እንደ መራህያን ይገባሉ

Geez Language

፪.፪.፪. የአመላች ቅጽሎችና የመራሕያን ልዩነት

አመላካች ቅጽሎች ለተሳቢ ስም ሲቀጸሉ እና እራሳቸው ተሳቢ ሲሆኑ የመጨረሻቸውን ፊደል ወደ ግእዝና ሳብዕ ፊደል ይለውጣሉ

ዝ ፣ ዝንቱ የነበረው ዘ ፣ ዘንተ ይሆናል

ዝኩ ፣ ዝስኩ ፣ ዝክቱ የነበረው ዝኮ ፣ ዝስኮ ፣ ዝክተ ይሆናል (በቅደም ተከተል ነው)

እሎንቱ---እሎንተ

ዛ ፣ ዛቲ---ዛ ፣ ዛተ

እንትኩ ፣ እንታክቲ--እንትኮ ፣ እንታክተ

እላ ፣ እላንቱ---እላ ፣ እላንተ

ለምሳሌ ፡-

እቀብ ዛተ ሀገረ--ይህችን አገር ጠብቅ

ኢይሰቲ ዘንተ ማየ--ይህን ውሃ አልጠጣም

ለእመ በላዕክሙ እንትኮ በለሰ ሞተ ትመውቱ--ያችን በለስ በበላችሁ ጊዜ ሞትን ትሞታላችሁ

በምሳሌው መሠረት ሌሎችንም መጠቀም ይቻላል

አሥሩ መራሂያን ግን ተሳቢ መሆንም ሆነ ለተሳቢ መቀጸል ስለማይችሉ እነሱን ተክቶ ለተሳቢ የሚቀጸልና ተሳቢ የሚሆን ‹‹ኪያሁ--እርሱን››ነው

ምሳሌ ፡-አፍቀርኩ ኪያሁ ፣ ኪያከ ፣ ኪያሆሙ ፣ ኪያክሙ ፣ ኪያሃ ፣ ኪያኪ ፣ ኪያሆን ፣ ኪያክን ፣ ኪያየ ፣ ኪያነ እያለ በ10ሩ መራሂያን ይነገራል ።

፪.፫. ወገናዊ ቅጽሎች

የወገን ነገር ከዚህ ይነገራል ። ወገን የሚሆኑ ፡- የሰው ፣ የሀገር ስም ፣ ነባር ፣ ሰዋሰው ናቸው ። የመድረሻውን ቀለም ራብዕ ያደርጋሉ ። ወገን ሲገባም ያልተባበረ ነው ። ያዕቆባዊ ዕብራዊ ይላ ። ላዕላይ ሲል እንደ ዊ ሣልሱ ቢሆን በቀና ነበር ። መምህራን ተባብረውበት ነው እንጂ ። በዝርዝር ቃል ቀዳማዩሁ ሲል ሳልሱ ነው ።

ክፍል ሦስት

ዘርፍ አየያዥ ፣ዘርፍ ደፊ ፣ ዘርፍ ጠምዛዥ

፫.፩. ዘርፍ አየያዥና ዘርፍ ደፊ

ዘ ፣እንተ ፣ እለ ፣ ለ ፣ ተናባቢ(ዘርፍ)

- ዘ= ለአንድ ለብዙ
- እንተ= ለነጠላ ብቻ
- እለ=ለብዙ
- ለ=ለአንድ ለብዙ (በዝርዝር)
- ተናባቢ= ለአንድ ለብዙ

.ለ. ለ ፣ዘ ፣ ተናባቢ(ዘርፍ) ፡-

‹‹ለ››

ቤቱ ለአብርሃም

⇒ የአብርሃም ቤት

ለአብርሃም ቤቱ

‹‹ዘ››

ቤት ዘአብርሃም

የአብርሃም ቤት

ዘአብርሃም ቤት

Geez Language

‹‹ተናባቢ(ዘርፍ)››

ቤተ አብርሃም= የአብርሃም ቤት

‹‹እንተ››

ደመና እንተ ሰማይ
እንተ ሰማይ ደመና — **የሰማይ ደመና**

ደመናት እለ ሰማይ
እለ ሰማይ ደመናት — **የሰማይ ደመናዎች**

፫.፪. ዘርፍ ጠማዛዥ

ዘ ፣እንተ ፣ እለ

ዘ= አምላክ ንጉሠ ዘሰማይ መንበር= የሰማይ የዙፋን ንጉሥ አምላክ
እንተ= ሳይዳ ዕቅብተ እንተ ክብር ድንግልና=የክብር ድንግልናን የጠበቀች ቆንጆ
እለ= ኖሎት ዐቀብተ እለ ጎል እንስሳ= የበረት እንስሶችን የሚጠብቁ እረኞች

Geez Language

ክፍል አራት

ዝርዝር ፣ ገቢርና ተገብሮ


፬.፩. ዝርዝር ፣ገቢርና ተገብሮ

መራሕያን	ምሳሌ = ቤት ፣ ቅዳሴ	ተርጉም ዘንተ
ውእቱ	ቤቱ=ቤቱ/ቤቶ=ቤቱን/	ቅዳሴሁ=
አንተ	ቤትከ=ቤትህ/ቤተከ= ቤትህን	ቅዳሴከ=
ውእቶሙ	ቤቶሙ=ቤታቸው/ቤታቸውን/	ቅዳሴሆሙ=
አንትሙ	ቤትክሙ=ቤታችሁ/ቤተክሙ=ቤታችሁን	ቅዳሴክሙ=
ይእቲ	ቤታ=ቤቷ/ቤቷን/	ቅዳሴሃ=
አንቲ	ቤትኪ= ቤትሽ/ቤተኪ=ቤትሽን	ቅዳሴኪ=
ውእቶን	ቤቶን=ቤታቸው/ቤታቸውን/	ቅዳሴሆን=
አንትን	ቤትክን=ቤታችሁ/ቤተክን=ቤታችሁን	ቅዳሴክን=
አነ	ቤትየ=ቤቴ/ቤቴን/	ቅዳሴየ=
ንሕነ	ቤትነ=ቤታችን/ቤተነ=ቤታችንን	ቅዳሴነ=

- ሀረግ ፡- ምሳሌ = እንዘ የሐውር ኀበ ቤቱ
  ቅዱስ ሙሴ
  ጊዜ መጽአ ወልድ
  እመ መጻእከ ቤተ ትምህርት
  ዘተቀደሰ አብሃም


Geez Language

❖ ዐረፍተ ነገር ፡-



ምሳሌ ፡- ቅዱስ አብርሃም ወለደ ቅዱሰ ይስሐቅሀ ፡ ፡ አው

አብርሃም ቅዱስ ወለደ ይስሐቅሀ ቅዱሰ ፡ ፡



ምሳሌ ፡- ወለደ ቅዱስ አብርሃም ቅዱሰ ይስሐቅሀ ፡ ፡ አው

ወለደ አብርሃም ቅዱስ ይስሐቅሀ ቅዱሰ ፡ ፡

<u>ካልአን ምሳሌያተ ዓረፍተ ነገር</u>

እንዘ የሐውር ጎበ ቤቱ ረከብክዎ ፡ ፡

እመ መጻእከ ትረክበኒ ፡ ፡

በሊዓ ምስሓ ሆረት ጎበ ግብራ ፡ ፡

ቅዱስ ሙሴ ከፈለ ባሕረ ኤርትራ ፡ ፡

ጎበ ቤተ ትምህርት አሐውር ፡ ፡

ሀገር ቅድስት ኢትዮጵያ ፡ ፡

ኮሉ ይርእድ ጊዜ መጽአ ወልድ ፡ ፡

ዘተቀደሰ አብርሃም ወለደ ይስሐቅሀ ቅዱሰ ፡ ፡

ዘተፃብአ ምስለ ቢፁ ዘአበሰ ፡ ፡

Geez Language

፬.፪. የአካል ክፍሎች

ግዕዝ ትርጓሜ	ግዕዝ ትርጓሜ	ግዕዝ ትርጓሜ
ገጽ---ፊት	----------ዳሌ	ሕንብርት-----እንብርት
ርእስ----ራስ	ቀኑይጽ------ጭን	ሰማሕ-------ጣፊያ
ሥእርት---ጸጉር	እግር-------እግር	እራኅ-------መሐል እጅ
ድምድማ-----ጎፈሬ	ብርክ-----ጉልበት	ቃል---------ቃል
ጽፍሮ--------ሹርባ	ሰኰና-----ተረከዝ	እስትንፋስ ----ትንፋሽ
ፍጽም---------ግንባር	ምክያድ---ጫማ	ማእስ---------ቆዳ
እዝን----------ጆሮ	ልሳን---- -ምላስ	ድማህ-------መሀል ራስ
ዐይን----------ዐይን	ልብ---------ልብ	ህፍን----------መዳፍ
አንፍ---------አፍንጫ	ቅርንብ------ቅንድብ	አምትንት--------ጅማት
መልታሕት---ጉንጭ	ሐሞት------ሐሞት	አፅም----------አጥንት
ጽህም----------ጢም	መሌሊት-----ብልት	አጽመ-ገቦ------ጎን አጥንት
ሕልቅ----------አገጭ	ማዑት-----አንጀት	ስን-----ደምግባት(¨ን¨አይጠብቅም)
ክሳድ----------አንገት	ሲበት--------ሽበት	ሕሊና----------ሀሳብ
መትከፍት------ትክሻ	ሰንቡዕ------ሳንባ	ሀቄ----------ወገብ
እድ----------እጅ	ኩላሊት-----ኵላሊት	ዓኒን----------ቆለጥ
መዝራእት------ክንድ	ማሕጸን------ቤተ ጽንስ	ከርሥ/ከብድ----ሆድ
እመት----------ክንድ	ስን-----ጥርስ(¨ን¨ይጠብቃል)	ከንፈር----------ከንፈር
አጽባዕት------እጣት	ቆናዝልዕ-----ቁንጮ	ሕፅን----------ጡጦት
መንኰብ-አውራጣት	ኩርናዕ--የክንድ ኩማ	ቀልደድ----ሽፋፍት
ዘባን----------ጀርባ	ጉርኤ---------ጉሮሮ	ካዕሴ----------ሰንበር
እንግድዓ-----ደረት	መንሰክ--------መንጋጋ	ሰኮም----------አንጎል
ጥብ----------ጡት	መስቴካ--------ጨንጓራ	ፅንስ/ሰይል-------ፅንስ
ገቦ----------ጎን	ንዋየ ውስጥ-----የሆድ እቃ	ሰፈርጐ(ኰ)ል-----እንቅርት

Geez Language

፬.፫. ርብሐ የዋህ ወመሠርይ ግስ

ሀ. ቀዳማይ አንቀጽ ፣ ለ. ካልዓይ አንቀጽ ፣ ሐ. ዘንድ አንቀጽ ፣ መ. ትእዛዝ አንቀጽ

ግስ፡-ገዘመ[ቀተ]፡ ቆረጠ (የዛፍ) በየዋህ፡-በተደራጊ ፣ በአስደራጊ እና በአደራራጊ

፩.በተደራጊ

መራሕያን	ቀዳማይ	ትርጓሜ	ካልዓይ	ትርጓሜ	ዘንድ	ትርጓሜ	ትእዛዝ	ትርጓሜ
ውእቱ	ገዘመ	ቆረጠ	ይገዝም	ይቆርጣል	ይግዝም	ይቆርጥ ዘንድ	ይግዝም	ይቁረጥ
አንተ	ገዘምከ	ቆረጥክ	ትገዝም	ትቆርጣለህ	ትግዝም	ትቆርጥ ዘንድ	ግዝም	ቁረጥ
ውእቶሙ	ገዘሙ	ቆረጡ	ይገዝሙ	ይቆርጣሉ	ይግዝሙ	ይቆርጡ ዘንድ	ይግዝሙ	ይቁረጡ
አንትሙ	ገዘምክሙ	ቆረጣችሁ	ትገዝሙ	ትቆርጣላችሁ	ትግዝሙ	ትቆርጡ ዘንድ	ግዝሙ	ቁረጡ
ይእቲ	ገዘመት	ቆረጠች	ትገዝም	ትቆርጣለች	ትግዝም	ትቆርጥ ዘንድ	ትግዝም	ትቁረጥ
አንቲ	ገዘምኪ	ቆረጥሽ	ትገዝሚ	ትቆርጫለሽ	ትግዝሚ	ትቆርጪ ዘንድ	ግዝሚ	ቁረጪ
ውእቶን	ገዘማ	ቆረጡ	ይገዝማ	ይቆርጣሉ	ይግዝማ	ይቆርጡ ዘንድ	ይግዝማ	ይቁረጡ
አንትን	ገዘምክን	ቆረጣችሁ	ትገዝማ	ትቆርጣላችሁ	ትግዝማ	ትቆርጡ ዘንድ	ግዝማ	ቁረጡ
አነ	ገዘምኩ	ቆረጥኩ	እገዝም	እቆርጣለሁ	እግዝም	እቆርጥ ዘንድ	እግዝም	ልቁረጥ
ንሕነ	ገዘምነ	ቆረጥን	ንገዝም	እንቆርጣለን	ንግዝም	እንቆርጥ ዘንድ	ንግዝም	እንቁረጥ

Geez Language

፪.በአስደራጊ

መራሕያን	ቀዳማይ	ትርጓሜ	ካልዓይ	ትርጓሜ	ዘንድ	ትርጓሜ	ትእዛዝ	ትርጓሜ
ውእቱ	አግዘመ	አስቆረጠ	ያገዝም	ያስቆርጣል	ያግዝም	ያስቆርጥ ዘንድ	ያግዝም	ያስቆርጥ
አንተ	አግዘምከ	አስቆረጥክ	ታገዝም	ታስቆርጣለህ	ታግዝም	ታስቆርጥ ዘንድ	ኣግዝም	አስቆርጥ
ውእቶሙ	አግዘሙ	አስቆረጡ	ያገዝሙ	ያስቆርጣሉ	ያግዝሙ	ያስቆርጡ ዘንድ	ያግዝሙ	ያስቆርጡ
አንትሙ	አግዘምክሙ	አስቆረጣችሁ	ታገዝሙ	ታስቆርጣላችሁ	ታግዝሙ	ታስቆርጡ ዘንድ	ኣግዝሙ	አስቆርጡ
ይእቲ	አግዘመት	አስቆረጠች	ታገዝም	ታስቆርጣለች	ታግዝም	ታስቆርጥ ዘንድ	ታግዝም	ታስቆርጥ
አንቲ	አግዘምኪ	አስቆረጥሽ	ታገዝሚ	ታስቆርጫለሽ	ታግዝሚ	ታስቆርጪ ዘንድ	ኣግዝሚ	አስቆርጪ
ውእቶን	አግዘማ	አስቆረጡ	ያገዝማ	ያስቆርጣሉ	ያግዝማ	ያስቆርጡ ዘንድ	ያግዝማ	ያስቆርጡ
አንትን	አግዘምክን	አስቆረጣችሁ	ታገዝማ	ታስቆርጣላችሁ	ታግዝማ	ታስቆርጡ ዘንድ	ኣግዝማ	አስቆርጡ
አነ	አግዘምኩ	አስቆረጥኩ	ኣገዝም	አስቆርጣለሁ	ኣግዝም	አስቆርጥ ዘንድ	ኣግዝም	ላስቆርጥ
ንሕነ	አግዘምነ	አስቆረጥን	ናገዝም	እናስቆርጣለን	ናግዝም	እናስቆርጥ ዘንድ	ናግዝም	እናስቆርጥ

Geez Language !

፫.በአደራራጊ

መራሕያ	ቀዳማይ	ትርጓሜ	ካልዓይ	ትርጓሜ	ዘንድ	ትርጓሜ	ትእዛዝ	ትርጓሜ
ውእቱ	አስተጋዘመ	አቆራረጠ	ያስተጋዝም	ያቆራርጣል	ያስተጋዝም	ያቆራርጥ ዘንድ	ያስተጋዝም	ያቆራርጥ
አንተ	አስተጋዘምከ	አቆራረጥክ	ታስተጋዝም	ታቆራርጣለህ	ታስተጋዝም	ታቆራርጥ ዘንድ	ኣስተጋዝም	አቆራርጥ
ውእቶሙ	አስተጋዘሙ	አቆራረጡ	ያስተጋዝሙ	ያቆራርጣሉ	ያስተጋዝሙ	ያቆራርጡ ዘንድ	ያስተጋዝሙ	ያቆራርጡ
አንትሙ	አስተጋዘምክሙ	አቆራረጣችሁ	ታስተጋዝሙ	ታቆራርጣላችሁ	ታስተጋዝሙ	ታቆራርጡ ዘንድ	ኣስተጋዝሙ	አቆራርጡ
ይእቲ	አስተጋዘመት	አቆራረጠች	ታስተጋዝም	ታቆራርጣለች	ታስተጋዝም	ታቆራርጥ ዘንድ	ታስተጋዝም	ታቆራርጥ
አንቲ	አስተጋዘምኪ	አቆራረጥሽ	ታስተጋዝሚ	ታቆራርጫለሽ	ታስተጋዝሚ	ታቆራርጪ ዘንድ	ኣስተጋዝሚ	አቆራርጪ
ውእቶን	አስተጋዘማ	አቆራረጡ	ያስተጋዝማ	ያቆራርጣሉ	ያስተጋዝማ	ያቆራርጡ ዘንድ	ያስተጋዝማ	ያቆራርጡ
አንትን	አስተጋዘምክን	አቆራረጣችሁ	ታስተጋዝማ	ታቆራርጣላችሁ	ታስተጋዝማ	ታቆራርጡ ዘንድ	ኣስተጋዝማ	አቆራርጡ
አነ	አስተጋዘምኩ	አቆራረጥኩ	ኣስተጋዝም	አቆራርጣለሁ	ኣስተጋዝም	አቆራርጥ ዘንድ	ኣስተጋዝም	ላቆራርጥ
ንሕነ	አስተጋዘምነ	አቆራረጥን	ናስተጋዝም	እናቆረርጣለን	ናስተጋዝም	እናቆራርጥ ዘንድ	ናስተጋዝም	እናቆራረጥ

Geez Language

ቀተለ ፣ አጥመቀ ፣ ጎደገ ፣ ባረከ በቀዳማይ

መራሕያን	ለውእቱ	ለአንተ	ለውእቶሙ	ለአንትሙ	ለይእቲ	ለአንቲ	ለውእቶን	ለአንትን	ለንሕነ
ውእቱ	ቀተለ አጥመቀ ጎደጎ ባረከ	ቀተለከ	ቀተሉሙ አጥመቁሙ ጎደጉሙ ባረኩሙ	ቀተለክሙ	ቀተላ አጥመቃ ጎደጋ ባረካ	ቀተለኪ	ቀተሉን አጥመቁን ጎደጉን ባረኩን	ቀተለክን	ቀተለነ አጥመቀነ ጎደገነ ባረከነ
አንተ	ቀተልከ አጥመቆ(ጠ) ጎደጎ(ጠ) ባረኮ(ጠ)		ቀተልኮሙ አጥመቆሙ ጎደጎሙ ባረኮሙ		ቀተልካ አጥመቃ ጎደጋ ባረካ		ቀተልኮን አጥመቅን ጎደግን ባረክን		ቀተልክነ አጥመቀነ ጎደገነ ባረከነ
ውእቶሙ	ቀተልዎ	ቀተሉከ	ቀተልዎሙ	ቀተሉክሙ	ቀተልዋ	ቀተሉኪ	ቀተልዎን	ቀተሉክን	ቀተሉነ
አንትሙ	ቀተልክምዎ አጥመቅምዎ ጎደግምዎ ባረክምዎ		ቀተልክምዎሙ አጥመቅምዎሙ ጎደግምዎሙ ባረክረምዎሙ		ቀተልክምዋ አጥመቅምዋ ጎደግምዋ ባረክምዋ		ቀተልክምዎን አጥመቅምዎን ጎደግምዎን ባረክምዎን		ቀተልክሙነ አጥመቅሙነ ጎደግሙነ ባረክሙነ

Geez Language

ይእቲ	ቀተለቶ	ቀተለተከ	ቀተለቶሙ	ቀተለተክሙ	ቀተለታ	ቀተልኪያ	ቀተለቶን	ቀተለተክን	ቀተለተነ
አንቲ	ቀተልኪዮ አጥመቂዮ ጎደጊዮ ባረኪዮ		ቀተልኪዮሙ አጥመቂዮሙ ጎደጊዮሙ ባረኪዮሙ		ቀተልኪያ አጥመቂያ ጎደጊያ ባረኪያ		ቀተልኪዮን አጥመቂዮን ጎደጊዮን ባረኪዮን		ቀተልክነ አጥመቅነ ጎደሽ ባረክነ
ውእቶን	ቀተላሁ	ቀተላከ	ቀተላሆሙ	ቀተላክሙ	ቀተላሃ	ቀተላኪ	ቀተላሆን	ቀተላክን	ቀቀተላነ
አንትን	ቀተልክናሁ አጥመቅናሁ ጎደግናሁ ባረክናሁ		ቀተልክናሆሙ አጥመቅናሁ ጎደግናሁ ባረክናሁ		ቀተልክናሃ አጥመቅናሃ ጎደግናሃ ባረክናሃ		ቀተልክናሆን አጥመቅናሆን ጎደግናሆን ባረክናሆን		ቀተልክናነ
አነ	ቀተልክዎ	ቀተልኩከ	ቀተልክዎሙ	ቀተልኩክሙ	ቀተልክዋ	ቀተልኩኪ	ቀተልክዎን	ቀተልኩክን	
ንሕነ	ቀተልናሁ	ቀተልናከ	ቀተልናሆሙ	ቀተልናክሙ	ቀተልናሃ	ቀተልናኪ	ቀተልናሆን	ቀተልናክን	

Geez Language

ከፈለ--ከፈለ ከቀዳማይ እስከ ዘንድ

መራሕያን	ለውእቱ ቀዳማይ ካልአይ ዘንድ ትእዛዝ	ለአንተ ቀዳማይ ካልአይ ዘንድ ትእዛዝ	ለውእቶሙ ቀዳማይ ካልአይ ዘንድ ትእዛዝ	ለአንትሙ ቀዳማይ ካልአይ ዘንድ ትእዛዝ	ለይእቲ ቀዳማይ ካልአይ ዘንድ ትእዛዝ	ለአንቲ ቀዳማይ ካልአይ ዘንድ ትእዛዝ	ለውእቶን ቀዳማይ ካልአይ ዘንድ ትእዛዝ	ለአንትን ቀዳማይ ካልአይ ዘንድ ትእዛዝ	ለአነ ቀዳማይ ካልአይ ዘንድ ትእዛዝ	ለንሕነ ቀዳማይ ካልአይ ዘንድ ትእዛዝ
ውእቱ	ከፈሎ ይከፍሎ ይክፍሎ ይክፍሎ	ከፈለከ ይከፍለከ ይክፍልከ	ከፈሎሙ ይከፍሎሙ ይክፍሎሙ	ከፈለክሙ ይከፍለክሙ ይክፍልክሙ	ከፈላ ይከፍላ ይክፍላ	ከፈለኪ ይከፍለኪ ይክፍልኪ	ከፈሎን ይከፍሎን ይክፍሎን	ከፈለክን ይከፍለክን ይክፍልክን	ከፈለኒ ይከፍለኒ ይክፍለኒ	ከፈለነ ይከፍለነ ይክፍለነ
አንተ	ከፈልኮ ትከፍሎ ትክፍሎ ክፍሎ		ከፈልሙ ትከፍሙ ትክፍሙ ክፍሎሙ		ከፈልካ ትከፍላ ትክፍላ ክፍላ		ከፈልኮን ትከፍሎን ትክፍሎን ክፍሎን		ከፈልከኒ ትከፍለኒ ትክፍለኒ ክፍለኒ	ከፈልከነ ትከፍለነ ትክፍለነ ክፍለነ
ውእቶሙ	ከፈልዎ ይከፍልዎ ይክፍልዎ	ከፈሉከ ይከፍሉከ ይክፍሉከ	ከፈልዎሙ ይከፍልዎሙ ይክፍልዎሙ	ከፈሉክሙ ይከፍሉክሙ ይክፍሉክሙ	ከፈልዋ ይከፍልዋ ይክፍልዋ	ከፈሉኪ ይከፍሉኪ ይክፍሉኪ	ከፈልዎን የከፍልዎን ይክፍልዎን	ከፈሉክን ይከፍሉክን ይክፍሉክን	ከፈሉኒ ይከፍሉኒ ይክፍሉኒ	ከፈሉነ ይከፍሉነ ይክፍሉነ

Geez Language!

አንትሙ	ከፈልክምዎ ትከፍልዎ ትክፍልዎ ክፍልዎ		ከፈልክምዎ ሙ ትከፍልዎሙ ትክፍልዎሙ ክፍልዎሙ		ከፈልክምዋ ተከፍልዋ ትክፍልዋ ክፍልዋ		ከፈልክምዎን ትከፍልዎን ትክፍልዎን ክፍልዎን		ከፈልክሙኒ ትከፍሉኒ ትክፍሉኒ ክፍሉኒ	ከፈልክ ሙነ ትከፍሉነ ትክፍሉነ ክፍሉነ
ይእቲ	ከፈለቶ ትከፍሎ ትክፍሎ	ከፈለተከ ትከፍለከ ትክፍልከ	ከፈለቶሙ ትከፍሎሙ ትክፍሎሙ	ከፈለተክሙ ትከፍለክሙ ትክፍልክሙ	ከፈለታትከ ፍላትክፍላ	ከፈለተኪ ትከፍለኪ ትክፍልኪ	ከፈለቶን ትከፍሎን ትክፍሎን	ከፈለተክን ትከፍለክን ትክፍልክን	ከፈለተኒ ትከፍለኒ ትክፍለኒ	ከፈለተነ ትከፍለነ ትክፍለነ
አንቲ	ከፈልኪዮ ትከፍሊዮ ትክፍሊዮ ክፍሊዮ		ከፈልኪዮሙ ትከፍሊዮሙ ትክፍሊዮሙ ክፍሊዮሙ		ከፈልኪያ ትከፍሊያ ትክፍሊያ ክፍሊያ		ከፈልኪዮን ትከፈሊዮን ትክፍሊዮን ክፍሊዮን		ከፈልክኒ ትከፍልኒ ትክፍልኒ ክፍልኒ	ከፈልክነ ትከፍልነ ትክፍልነ ክፍልነ
ውእቶን	ከፈላሁ ይከፍላሁ ይክፍላሁ	ከፈላከ ይከፍላከ ይክፍላከ	ከፈላሆሙ ይከፍላሆሙ ይክፍላሆሙ	ከፈላክሙ ይከፍላክሙ ይክፍላክሙ	ከፈላሃ ይከፍላሃ ይክፍላሃ	ከፈላኪ ይከፍላኪ ይክፍላኪ	ከፈላሆን የከፍላሆን ይክፍላሆን	ከፈላክን ይከፍላክን ይክፍላክን	ከፈላኒ ይከፍላኒ ይክፍላኒ	ከፈላነ ይከፍላነ ይክፍላነ
አንትን	ከፈልክናሁ ትከፍላሁ ትክፍላሁ ክፍላሁ		ከፈልክናሆ ሙ ትከፍላሆሙ ትክፍላሆሙ ክፍላሆሙ		ከፈልክናሃ ትከፍላሃ ትክፍላሃ ክፍላሃ		ከፈልክናሆን ትከፍላሆን ትክፍላሆን ክፍላሆን		ከፈልክናኒ ትከፍላኒ ትክፍላኒ ክፍላኒ	ከፈልክና ነ ትከፍላላነ ትክፍላነ ክፍላነ
አነ	ከፈልክዎ እከፍሎ እክፍሎ	ከፈልኩከ እከፍለከ እክፍልከ	ከፈልክዎሙ እከፍሎሙ እክፍሎሙ	ከፈልኩክሙ እከፍለክሙ እክፍልክሙ	ከፈልክዋ እከፍላ እክፍላ	ከፈልኩኪ እከፍለኪ እክፍልኪ	ከፈልክዎን እከፍሎን እክፍሎን	ከፈልኩክን እከፍለክን እክፍልክን		

Geez Language

ንሕነ	ከፈልናሁ ንከፍሎ ንክፍሎ	ከፈልናከ ንከፍለከ ንክፍልከ	ከፈልናሆሙ ንከፍላሆሙ ንክፍሎሙ	ከፈልናክሙ ንከፍለክሙን ክፍልክሙ	ከፈልናሃ ንክፍላ ንክፍላ	ከፈልናኪ ንክፍለኪ ንክፍልኪ	ከፈልናሆንክ ፍሎን ንክፍሎን	ከፈልናክን ንክፍላክን ንክፍላክን		

Geez Language I